# <u>ትግል ለሥልጣን እንጂ የመስፍንን ጎፈሬ ለማበጠር?</u>

# ያውም የአርበኛ ጉተና ባልሆነበት!

ከ ፡ ሀይለ ገብርኤል ጤና

በ ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ የፖለቲካ መሀይምነት መስፈኑ አንድና ሁለት በሉኝ የሚል አይደለም ። ከሶሻሊስቱ ጎራ መፈራረስ በኋላ፤በኢራን የኮሜይኒ አገዛዝ ሰፍኖ አክራሪነት ከተሰራጨም በኋላ፤የአንድ ሀያል መንግስት አዲስ የዓለም ቅኝት ከተባለ በኋላ ሁሉም ወደ ጨለመ አቅዋም፤አክራሪነት፤ጽንፈኛነትና ሽንፈተኝነት ማምራቱ የታየ ነው ። የሰው በላው ስርዓት አዳናቂዎች መወራጨትና መፈንጨት ሲጀምሩ፤ ካፒታሊዝም ወይ ሞት ባዮች ሲበረክቱ፤ ማንበብ ማወቅ ሀጢያት ሆኖ አላዋቂ ሳሚና ለፍላፊ መድረክ ሲያጣብብ ፤ ይሉኝታ ከአለማወቅ ጋር ተጎዳኝቶ ሲተን ፤ በፈረንጅ ሽልማትና ዲግሪ መመጻደቅ ብልህነት ሆኖ ሲውገረገር የፖለቲካ መሀይሞችና የበሸቀጡ አድርባዮች አንቱ ተብለው የፖለቲካውን መድረክ በውልግድ አቅዋማቸው ሲያጨቀዩ መታዘቡ ሊያስገርመን አይገባም ።

ከዘመኑ የፖለቲካ መሃይሞች አንዱ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም የሚባሉት ግለሰብ ናቸው ። የአድርባይ አድርባይ፤ ጨፈታ፤ ጣሽ፤ ድርምቢታም፤ አባ ለከርሱ ሆነው ቆይተዋል ። ላምያውቅሽ ታጠኚ ሆኖ ምሁር፤አዋቂና አልፎም ሀገር ወዳድና ጸረ ወያኔም ሊሏቸው የሚከጅሉም ጥቂቶች አይደሉም ። ድሮም ባልዘፈንሽ የሆነባቸው የማይችሉትን ስምሪት ጀመርን ያሉ ደግሞ ወገቤን ሲሉ መስፍንን ይዘው ደፋ ቀና በማለት ኪሳራቸውን ለማረሳሳት እየጣሩ ናቸው ። አንዳንድ የዋሆችና ልድገመውና የፖለቲካ መሀይሞች ፕሮፌሰር መስፍን ከአሜሪካ ጋር ያላቸውን የሚሸትና የሚወገዝ ግንኙነት አንቀበልም ይላሉ ። ውርድ ከእኛ ። የአሜሪካንን የሰላም ጓድ/ፒስ ኮር/ ሚና ካጅ ሆነው ሲፋለሙ የነበሩትን የማያውቁ ናቸው ። የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ታገል መጽሄታቸውን ለማውጣት አማካሪ ያስፈልጋችኋል ሲባሉ ፕሮፌሰሩን ጠይቀው እሳቸው ፈርተው እምቢ ማለታቸውን ያምያውቁ ናቸው ። ወይም መርሳቱን የመረጡ ። አጼው ወደ ደቡብ በአውራጃ ገገዢነት ሲልኩኡአቸው ለምነውና ተለማምጠው ምቅረታቸውን የማያውቁ ናቸው ፡፤ ማን ነበር የደርግ መርማሪ ኮሚሽን ሆኖ እነ አክሊሉ ሀብተ ወልድን ያስለቀሰ? ማን ነበረ ለደርግ ጠመንጃ ይዛችኋልና እርምጃ ውሰዱ ብሎ ለ 60ዎቹ መረሸን ድጋፍ የሰጠ ? ማነው ለመለስ በለደንም በአዲስ አበባ ሙሉ ድጋፍ ሰጥቶ ታጋዮችን ደም የጠማቸው ብሎ ያወገዘ? ፕሮፌሰር አስራት ግንጠላን እምቢ ሲሉ መስፍን የት ነበር ? ስለዚህ ማፈሪያ ግለሰብ ተዘርዝሮ የማያልቅ ክስን ጸረ ሕዝብ ድርጊት መኖሩን መደበቅ አይቻልም ። ይህን ስጽፍ እሪ የሚሉ ተላሎች እንዳሉ ስቼ አይደለም --ግን የሀገር ጉዳይ ነውና ራስን ማታለልና የሀሰት ነቢይን ማመን ያላደግኩበት ስላልሆነ ነው ። ዴሞክራሲ በሀገር ቢሰፍን ፕሮፌሰር መስፍን ፍርድ ቀራቢ ናቸው ። ይህ ነው ሀቁ ተወደደም ተጠላ ።

የተነሳሁበት ዋና ጉዳይ ፕሮፌሰር መስፍን አዲስ መጽሃፍ ጻፍኩ ብለው በአሜሪካ የሚያደርጉትን ስብስርባ የሚምለከትና እሳቸው የለፈፉቱን መሰረት አድርገው ራሱን ይነገር ዓለሙ በሚል ሽፋን የደበቁ ቱልቱላዎች የጻፉትን በሚመለከት ነው ። ፕሮፌሰሩ በሄዱበት ሁሉ ኢሕአፓን ማውገዝ ላይ አተኩረው የነበረ ሲሆን ይህን በተመለከተ መልስ ሊሰጣቸው የሚችለው ድርጅቱ በመሆኑ ወደዚያ አልገባም ። አርበኞቻችንንም የሞተ ጣሊያን ጠቅሰው ባንዳ ሊሉ መቃታቸውንም ዜጋ ሁሉ አውግዞ ሊያወድቅባቸው የሚገባ ነው ። ፕሮፌሰሩ አንዴም ቆራጦች በዋሉበት ያልዋሉ ፈሪ በመሆናቸው ጀግኖችን ማከቸልቸል የኢምንት ሰዎች የተለመደ ጥረት ነውና በዚሁ ምረንዎታል ብለን ተሳልቀን የምናልፈው ነው ። ዜጎች

መርሳት የሌልባቸ ነፍሰ ገዳዩን የወያኔው መሪ ክንፈ ሲሞት ኢትዮጵያ ሰው አጣች ማለታቸውን ነው ። አማራ የሚባል ሕዝብ የለም ማለታቸውን ነው ። መለስን ልጄ ማለታቸውን ነው ። ወደ ቁም ነገሩ ስንመለስ ፕሮፌሰሩ የደርግ አማካሪ ነበሩና ያን ደርግን የታገለውን ትውልድ በጣም ይጠላሉ ። ያረክሳሉ ያወግዛሉ ። ጻፍኩት ባሉት አዳፍኔ መጽሃፋቸው በጅምላ ያን ትውልድ ያወግዛሉ ። የስልጣን ጥመኛ ይሉታል ። ግድያ ያመጣም ይሉታል--የኢትዮጵያ ታሪክ በሰላማዊ ሽግግር የታወቀ ይመስል፤ ግድያና ፍጅትን ለየካቲቱ ትውልድ የፕሮፌሰሩ ትውልድና የበፊቶቹማ ያላወረሱት ይመስል ።ፕሮፌሰር መስፍን በጅምላ ያን ትውልድ ሲያወግዙ የሥልጣን ጥም የነበረውና አጥፊ ነው በሚልም ነው ። ለስልጣን መታገል ጥፋት ነው በሚል ማለት ነው ።

ለፕሮፌረሰሩ እናርዳቸውና፤ ለጭፍሮቻቸውና ለነይነገር እናስተምራቸውና የፖለቲካ ትግል ግቡ ስልጣን ነው ። ጎፈሬ ለማበጣር አይደለም፤ የቡከኑን ቀርቶ የአርበኛውንም ቢሆን ። ለዚህም ነው ትግል ለፖለቲካ ስልጣን እንጂ ለመስፍን ጎፈሬ ማበጠር አይደለም ያልነው ።

ለውጥ ባገር እማጣለሁ ብሎ፤ሕዝባዊ ነኝ ብሎ ትግል የተሰማራ ድርጅት ግቡ ስልጣን መያዝ ነው ። ለምን? ስልጣን ካልያዘ ለውጥ ማምጣት ስለማይችል ነው ። አንዳንድ ደንብራ ድርጅቶሽ ትግላችን ለስልጣን አይደለም ይሉን የለ? ታዲያ ትግላቸው ለምድር ነው ? ወያኔን ተለማምጠው ፍርፋሬ ሊጋሩ ካልሆነ ያለውን አገአዝ ጥሎ ስልጣን መመያዝ ግብ መሆን አለበት ። ያ ትውልድ ደሙን ያፈሰሰውና አሁንም የመንታገለው ለስልጣን ነው ። የኢትዮጵያን ሕዝብ የሥልጣኑ ባለቤት ለማድረግ አራት ነጥብ። አደናጋሪውን ፕሮፌሰር ተከትለው የቀባጠሩ ትግል ለዴሞክራሲ ነው ወይስ ለቤተ መንግስት ብለው ሊመጻድቁም ሞክረዋል ። ቤተ መንግስት ካልተገባ ወይም ስልጣን ካልተያዘ ለውጥን ማምጣት አይቻልም ። ትግል ለስልጣን እንጂ የፕሮፌሰርን ዋጋ ቢስ ጉተና ለማበጠር አይደለም ፡፤ ግን ስልጣን ስንል ለግለሰብና ለቡድን ጥቅም ሳይሆን የሕዝብን ዴሞክራሲያዊ ፍላጎት ለማሟላት ማለት ነው ። መሆንም አለበት። ያ ትውልድ ለስልጣን ታገለ ብሎ ለማውገዝ መነሳት ግን ፖለቲካ ባዶነትን ገላጭ ነው --ትግል ለስልጣን ነውና። ዋናው ጥያቄ ግን ስልጣን ለማን ስልጣን ለምን የሚለው ነው ። ፕሮፌሰር መስፍን ያ ትውልድ ሆነ ኢሕአፓ ለስልጣን ታገሉ ሲሉ እቅጩ ይነገር ሲባል አላዋቂነታቸውን ነው ግልጽ ያደረጉት ። ለስልጣን መታገል የሚጠበቅና መደረግም መሆንም ያለበት ነው ። ለስልጣን ካልታገልን ለዴሞክራሲ መታገል አንችልም ። እንዳልነው ትግል ለማን ስልጣን የሚለው ነው ።

ፕሮፌሰር መስፍን መለስ ብለው እስቲ ያንቡ ፤ ለመንቃት ይሞክሩ ። ትግል ለስልጣን እንጂ የርሶውን ጎፈሬ ለማበጠር አይደለም ።